የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሰኔ 13 2015

ቁጥር/REF NO: 81256/145/11

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አስተዳደር ማንዋል ስለመላክ ይመለከታል

የትምህርት ሚኒስቴር አንዱ የለውጥ አጀንዳ የሆነውና በ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረገው የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተናን ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

ከነዚህ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች መካከል የመውጫ ፈተናውን አስተዳደር በሚፈለገው የጥራት መጠን ለማከናወን ይቻል ዘንድ የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አስተዳደር ማንዋል ተዘጋጅቶ የጸደቀ በመሆኑ ለተግባራዊነቱ 12 ገጽ የያዘ ማንዋል ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈፃሚ
- ለከፍተኛ ት/ት ብቃትና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ

ትምህርት ሚኒስቴር

# የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አስተዳደር ማንዋል

ትምህርት ሚኒስቴር
ሰኔ 2015 ዓ.ም

## 1. መግቢያ

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፍኖተ-ካርታ ጥናት ምክረ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት የመጀመሪያ ድግሪ ምሩቃንን ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የመውጫ ምዘናን እንዲወስዱ በማድረግ፤ ከአገራዊ ኢኮኖሚ፤ ከቴክኖሎጂ ዕድገትና ከማኅበረሰቡ ፍላጎት ጋር እያደገ የሚሄድ ገበያ መር ስርዓት ትምህርት ቀርጾ ተግባራዊ ለማድረግ፤ ምሩቃን በእውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት የበቁ መሆን አለመሆናቸውን ከተቀመጠው የምሩቃን ፕሮፋይል ጋር በመመዘንና በማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርቱን ዘርፍ ጥራት በማስጠበቅ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ለማፍራት እየሰራ ይገኛል።

በዚህም መሠረት ከተቀመጠው የምሩቃን ፕሮፋይል ጋር በመመዘን ማረጋገጥ የሚቻለው ወጥና ተመሳሳይነት ያለው አገራዊ የቅድመ ምረቃ እጩ ተመራቂዎች የመውጫ ፈተና ተግባራዊ ማድረግ መቻል አንዱ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፈተና አስተዳደር አስፈፃሚዎች ምልመላ፣ ምደባና የተለያዩ ተግባርና ኃላፊነትን የሚመራበት አሰራር ለመዘርጋት የአፈፃፀም ማንዋል ተዘጋጅቷል። በመሆኑም በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተለያዩ አደረጃጀቶችን በመፍጠር ማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑና ባለድርሻ አካለት ምዘናውን በውጤታማነትና በጥራት ለመፈጸም በምዘና ሂደቱ ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባርና ኃላፊነት በመለየት እንዲገነዘቡ ለማድረግ የትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 919/2014 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 11 መሰረት ይህን የመውጫ ፈተና አስተዳደር ማኑዋል አዘጋጅቷል።

## 2. ዓላማ

### 2.1 ዋና ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዋነኛ ዓላማ የፈተና አስተዳደር ስራዎች የሚመራበትን ወጥ ስርዓት በመዘርጋት የፈተና አስተዳደር ስራን ውጤታማ ማድረግ ነው።

### 2.2 ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ. የፈተና አስፈጻሚዎች ምልመላ እና ምደባ በአፈፃፀም ማንዋሉ መሰረት በፍትኃዊነትና በጥራት እንዲፈጸም ያስችላል፣

ለ. መንግስት በፈተና አስተዳደር አፈፃፀም ስራ ላይ የሚውለው ሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግ ይረዳል፣



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሐ. የመውጫ ፈተና አስፈጻሚ አካላት መካከል የታወቀና ስኬት የሚያስገኝ መስመርና የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ያግዛል።

## 3. የማንዋሉ አስፈላጊነት

ይህ የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አስተዳደር ማንዋል ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ በሁሉም የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች የሚመረቁ ተማሪዎች ፈተናውን እንዲወስዱ በማድረግ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ የባለድርሻ አካላት ሚናቸውን በሚገባ ተረድተው የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለማስቻል ሲሆን ይህም እንደሀገር ወጥና ተመሳሳይነት ያለው የአፈታተን ሂደት (ስርዓት) ለመዘርጋትና ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ ያስችላል።

ከዚህ በተጨማሪም ተፈታኝ ተማሪዎች ያለምንም እንግልት መረጃዎች ቀድመው እንዲደርሷቸው በማድረግ ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ያስችላል። በፈተና ጣቢያነት የተመረጡ ተቋማትም ይህንን በመረዳት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ቀድመው እንዲያጠናቅቁ በማድረግ የፈተና አስተዳደር ሂደቱን በውጤታማነት ለመምራት ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

## 4. የዩኒቨርሲቲ ግብረ-ኃይል

4.1 ግብረ ኃይሉ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡

1. የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት (ሰብሳቢ)
2. የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች (አባል)
3. የካምፓስ ዲኖች (አባል)
4. ሬጅስትራር ኃላፊ (አባል)
5. የአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክተር (አባል)
6. የግቢ ጸጥታ ኃላፊ (አባል)
7. ስርዓተ ጾታ ዳይሬክተር (አባል)
8. የአካባቢው (ሪጅን) ኢትዮ ቴሌኮም ኃላፊ (ተወካይ)
9. የአካባቢው የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ኃላፊ (ተወካይ)
10. አካዳሚክ ፕሮግራም ዳይሬክተር (ጸሐፊ)

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

4.2 ግብረ ኃይሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. ፈተናዉ የሚመራበትን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

ለ. የተማሪዎችን ምዝገባ፣ የፈተና ቦታ ምደባ፣ የፈተና አወሳሰድና የፈተና ውጤት ገለጻን በሚመለከት ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበትና በቅንጅት ይሠራል፤ ያስተባብራል።

ሐ. በቅደመ ፈተና እና በፈተና አሰጣጥ ሂደት የመፈተኛ ክፍሎችና ኮምፒዩተሮች በሚፈለገው ጥራትና መጠን መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል።

መ. ሌሎች የፈተና አስተዳደር ቁሳቁሶች ለተፈታኞች ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈሊጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ሠ. የፈተና ዝግጅትና አሰጣጥ ሂደቱን የተሳለጠ ለማድረግ የተለያዩ የስራ ክፍሎችን ያሰማራል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣

ረ. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተጠሪ የሆኑ ግብረ-ኃይሎችና ንዑስ ግብረ-ኃይሎችን ያደራጃል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውንም ይወስናል፣ አፈጻጸማቸውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ በየጊዜው ይገመግማል።

ሠ. ከአንድ በላይ ግቢ ያላቸው ተቋማት ላይ ተጨማሪ የፈተና አስተባባሪዎችን በግቢ (ካምፓስ) ደረጃ ያዋቅራል፤ ያሰማራል፣ ይደግፋል።

## 5. የሎጂስቲክና ቴክኒክ ግብረ-ኃይል

5.1 ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው የመውጫ ፈተና ግብረ-ኃይል ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ወይም አስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚንዳት (ሰብሳቢ)
2. የአይ.ሲ.ቲ ዳይሬክተር (አባል)
3. ጠቅላላ አገልግሎት (አባል)
4. የዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ዳይሬክተር (አባል)
5. የግዢ ዳይሬክተር (ተአባል)
6. የዩኒቨርሲቲው ክሊኒክ ኃላፊ (አባል)
7. የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክተር (ፀሐፊ)



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

5.2 ግብረ-ኃይሉ በዩኒቨርሲቲው የአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ወይም አስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

ሀ. ስራው የሚመራበትን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታታላል።

ለ. በዩኒቨርሲቲው ያለውን የኮምፒዩተር አቅም በሙሉ ለፈተናው አገልግሎት እንዲውል ያመቻቻል፣

ሐ. በፈተና ወቅት በየቀኑ ጤናማና ሙሉ አገልግሎት የሚሰጡ ኮምፒዩተሮች መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፣

መ. በኮምፒዩተሮች ላይ Safe Exam Browser መጫኑን ያረጋግጣል፣

ሠ. በግቢ ውስጥ የመብራትና ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲኖር ያደርጋል።

ረ. የተማሪዎችን ቁጥር የሚመጥን የድንገተኛ ህክምና ክፍሎችንና አንቡላንሶችን ያዘጋጃል፣ ለሚፈጠር የጤና እክል ተፈታኞች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጋል፣ አገልግሎቶች በሚጠበቀው ደረጃ መኖሩን ያረጋግጣል።

ሰ. የፈተና አሰጣጥ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ጄኔሬተር፣ ነዳጅና ሌሎች ግብዓቶች ተሟልተው እንዲቀርቡ ያደርጋል። የማቋረጥ ችግር ሲገጥም ደግሞ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

ሸ. ከፈተና አሰጣጥ ስራ ጋር ተዛማጅ የሆኑና በተቋሙ ሊሟሉ የሚገባቸውን ቁሳቁሶች ያሟላል፣ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ቀ. ከአንድ በላይ ግቢ ያላቸው ተቋማት ላይ ተጨማሪ የፈተና አስተባባሪዎችን በግቢ (ካምፓስ) ደረጃ ያዋቅራል፤ ያሰማራል፣ ይደግፋል።

## 6. የሬጂስትራርና ፈተና አስተዳደር ግብረ-ኃይል

6.1 ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው የመውጫ ፈተና ግብረ-ኃይል ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚደንት (ሰብሳቢ)
2. አካዳሚክ ፕሮግራም ዳይሬክተር (አባል)
3. ኮሌጅ ዲኖች/ዳይሬክተሮች (አባል)
4. ስርዓተ ጾታ ዳይሬክተር (አባል)
5. አይ.ሲ. ቲ ባለሙያ (አባል)
6. ሬጅስትራር (ጸሐፊ)



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

6.2 ግብረ ኃይሉ በአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚደንት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. ስራው የሚመራበትን ዕቅድ ያዘጋጃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

ለ. የዩኒቨርሲቲውን የፈተና አሰጣጥና አስተዳደር በበላይነት ይመራል።

ሐ. የፈተና አስፈጻሚዎችን ይመለምላል፤ በዩኒቨርሲቲው አብይ ግብረ ኃይል አስጸድቆ ይመድባል፤

መ. በተመደቡለት የተፈታኝ ተማሪዎች ቁጥር ልክ መፈተኛ ክፍሎችና ኮምፒዩተሮች መዘጋጀታቸውን እና ለፈተና ምቹ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ. ለፈተና የተመደቡ ፈታኝ መምህራንና የአይነ ስውራን አንባቢዎችን በፈተና ክፍሎች ይደለድላል፣ ለስራው ውጤታማነት ተገቢ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ረ. ለሌሎች ልዩ ፍላጎት ለሚያስፈልጋቸው ተፈታኞች አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

ሰ. የፈተና ደህንነቱን ለመጠበቅ ከተደራጀው የጸጥታና ደህንነት ግብረ-ኃይል ጋር በትብብር ይሰራል፣

ሸ. ለፈተና አስፈጻሚዎችና ለተፈታኞች ተገቢውን ገለጻ ይሰጣል።

ቀ. የፈተና አስተዳደር ስራው ሰላማዊ እና ከደንብ መተላለፍ የፀዳ እንዲሆን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ችግር ሲፈጠር በተዋረድ ሪፖርት ያደርጋል፣

በ. የፈተና ደንብ ጥሰትን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይከላከላል፤ የደንብ ጥሰት ሲፈጸምም እርምጃ ይወስዳል።

ተ. ተፈታኞቸን በመፈተኛ ክፍል ይደለድላል፣ ይመድባል፣

ቸ. ከውጭ ለሚመጡ የሌላ ተቋማት ተፈታኞች የበርና ወደ ፈተና አዳራሽ መግቢያ ዝርዝር ያዘጋጃል፣

ኀ. ከአንድ በላይ ግቢ ያላቸው ተቋማት ላይ ተጨማሪ የፈተና አስተባባሪዎችን በግቢ (ካምፓስ) ደረጃ ያዋቅራል፤ ያሰማራል፣ ይደግፋል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## 7. የጸጥታና ደህንነት ግብረ-ኃይል

7.1 ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው የመውጫ ፈተና ግብረ-ኃይል ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. የዩኒቨርስቲው ጥበቃና ደህንነት ኃላፊ (ሰብሳቢ)
2. የዩኒቨርስቲው የፌዴራል ፖሊስ ኃላፊ (አባል)
3. የተማሪዎች አገልግሎት ዲን (አባል)
4. የጥበቃ ሽፍት ኃላፊዎች/ መሪዎች (አባል)
5. የዩኒቨርሲቲው የግቢ ፖሊስ ኃላፊ (ጸሐፊ)

7.2 የጸጥታና ደህንነት ግብረ-ኃይሉ በዩኒቨርሲቲው የጥበቃና ደህንነት ኃላፊ የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

ሀ. በፈተና ጣቢያ ደረጃ የሚያስፈልግ የፖሊስ ኃይል የተፈታኝ ተማሪ ቁጥርንና ያታን ታሳቢ አድርጎ የሚወሰን ይሆናል።

ለ. ከግቢው ተማሪ ውጭ ለሆኑ ተፈታኞች ለፈተና ወደ ተመደቡበት ዩኒቨርስቲ/ካምፓስ እንዲገቡ በተላከው ዝርዝር መሰረት እንዲገቡ ያደርጋል፤

ሐ. የጸጥታ ሥጋት ያለባቸው ቀጠናዎች ተጨማሪ ኃይል እንዲመደብ ያደርጋል።

መ. ፈተና የሚሰጥባቸውን ክፍሎች፣ ጄኔሬተሮች፣ ካሜራዎችና የኢንቴርኔት ማዕከላት የ24 ሰዓት ሙሉ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያደርጋል።

ሠ. ከሌሎች የፈተና አስተዳደር ግብረ ኃይል ጋር መረጃ ይለዋወጣል።

ረ. ተፈታኞች ወደ መፈተኛ ክፍል ሲገቡ በእጅና በመፈተሻ መሳሪያ (Metallic Detector) በአግባቡ እንዲፈተሽ ያደርጋል።

ሰ. ተፈታኞች ስልክን ጨምሮ ማንኛውንም የተከለከሉ ነገሮች ወደ መፈተኛ ክፍል ይዘው እንዳይገቡ ተገቢውን ፍተሻ ያደርጋል።

ሸ. ከመፈተኛ ክፍል ውጭ (በፈተና ጣቢያ ግቢና በዙሪያው) ያለውን ለፈተና አሰጣጡ ሂደት አዋኪ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ከሆነም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

ቀ. ከጣቢያ አስተባባሪው ጥያቄ ሲቀርብለት ብቻ ወደ መፈተኛ ክፍል በመግባት ሥርዓት ያስከብራል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

በ. የተከለከሉ ቁሳቁሶችና መሣሪያዎች በመፈተኛ ክፍሎች ውስጥና ዙሪያ እንዳይኖሩ ከሚመለከታቸው ጋር ይሰራል፣ ይከታተላል።
ኀ. ከአንድ በላይ ግቢ ያላቸው ተቋማት ላይ ተጨማሪ የፈተና አስተባባሪዎችን በግቢ (ካምፓስ) ደረጃ ያዋቅራል፤ ያሰማራል፣ ይደግፋል።

## 8. የፈተና አስፈጻሚዎች (Exam administrators)

የፈተና አስፈጻሚዎች ማለት ከፈተና አሰጣጡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የፈተና ሥራ አመራሮችና ባለሙያዎች የሚመለከት ሲሆን አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውም እንደሚከተለው ይሆናል።

### 8.1 የፈተና አስተባባሪ

በአንድ ግቢ ያሉ የኮምፒዩተር ብዛት ታሳቢ በማድረግ እስከ 500 ተፈታኝ ባለባቸው ቀናት ወይም ግቢ አንድ ዲን እና ከሁለት ያልበለጡ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች በአስተባባሪነት ይመደባሉ።
የፈተና አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲ ደረጃ ግብረ-ኃይል ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፦

ሀ. በፈተና ማዕከሉ እና ጣቢያዎች ውስጥ ለሚሰጡ ፈተናዎች በሙሉ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የፈተና አስተዳደሩን ስራ ሙሉ በሙሉ የሚመራ ይሆናል።
ለ. በየዕለቱ በፈተና ማዕከል ለተደለደሉ ተፈታኞች የሚበቃ ያክል ብዛት ያለው ከኢንተርኔት ጋር የተገናኙ የመፈተኛ ኮምፒውተሮች መኖራቸውን እና በአግባቡ የሚሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
ሐ. ለሱፐርቫይዘሮች፣ ፈታኞች፣ አንባቢዎችና ተፈታኞች በፈተና ጣቢያ ደረጃ አስፈላጊውን የፈተና አሰጣጥ ገለፃ ይሰጣል፤
መ. በጣቢያው ውስጥ ያሉ ፈታኞችንና ሱፐርቫይዘሮችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ በወቅቱ መፍትሔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ አፋጣኝ ውሣኔ ይሰጣል፤ ከአቅም በላይ ከሆነም ከማዕከል ግብረ ሃይል ጋር በመነጋገር ለተከሰተው ችግር አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፤



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ሠ. ማየት ለተሳናቸው ተፈታኞች በደንብ ማንበብና መልስ መስጠት የሚችሉ ፈታኞችን ወይም የእጅ እንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ተፈታኞች የተመደቡ ረዳት ጸሐፊዎችን ትክክለኛነታቸውን አረጋግጦ ይመድባል፣ ስራቸውንም በቅርበት እየተከታተለ ችግር ሲገጥም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣

ረ. በፈተና አሰጣጥ ወቅት በቀጥታ በፈተና አሰጣጡ ሂደት ከሚሳተፉ ሰዎች በስተቀር ወደ መፈተኛ ክፍሎች አካባቢ እንዳይገቡ ያደርጋል፤

ሰ. ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ያልተወጡ ፈታኞች ሲያጋጥሙ ወዲያውኑ ለቅርብ አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

ሸ. መፈተኛ ክፍሎችና ዙሪያቸው ተገቢው የደህንነት ፍተሻ የተደረገላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣

ቀ. ፈታኞችን፣ የአይነ ስውር ተፈታኝ አንባቢን ያስተባብራል፣ ወደ ስራ ያስገባል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

## 8.2 ፈታኝ

ለመውጫ ፈተና በፈታኝነት ተመልምለው የተመረጡ መምህራን ከሚያስተምሩበት ኮሌጅ ውጭ እንዲሰማሩ ይደረጋል።

ተጠሪነቱ ለፈተና አሰተባባሪ ሆኖ የሚከተሉት ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. በግቢው ውስጥ ያሉ የኮምፒዩተር ብዛትና የተፈታኝ ቁጥርን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ፈታኞች ይመደባሉ፣

ለ. አንድ ፈታኝ እስከ 50 የሚደርሱ ተፈታኝ ተማሪዎችን የሚፈትን ሆኖ በሰፊ ክፍሎች የሚፈትኑ መምህራን ደግሞ በዚሁ ስሌት መሰረት ይመደባሉ፤

ሐ. የፈተና ሥራን በተመደበበት የፈተና ጣቢያ የመፈተኛ ክፍል በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ የመፈተኛ ክፍል እና ተፈታኞች ለፈተና ስራ ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

መ. የመፈተኛ ክፍሎችና አዳራሾች የመያዝ አቅም መሰረት በማድረግ ግብረ ሃይሉ ተጨማሪ ፈታኝ ሊመድብ ይችላል።

ሠ. ተፈታኞች በምዝገባ ቁጥራቸው ቅደም ተከተል መሠረት መቀመጫቸውን ከያዙ በኋላ ኮምፒውተሮቻቸውን በመክፈት አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲሞሉ ያደርጋል፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

ረ. በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጀውን አቴንዳንስ በተፈታኞች አስፈርሞ ለሚመለከተው አካል ያስረክባል።

ሰ. ፈተናው ሲጀመርም መልሶቻቸውን በአግባቡ እየሰጡ ስለመሄዳቸው ይከታተላል፣ እየተዘዋወረ ይቆጣጠራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

ሸ. ማንኛውንም ዓይነት የፈተና ደንብ የተላለፈ ተፈታኝ ሲገጥመው ከሱፐርቫይዘሩ የግል የፈተና ደንብ መተላለፍ ችግሮች ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ በመውሰድ ሞልቶና ፈርሞ ለሱፐርቫይዘሩ ያቀርባል፤

ቀ. እንደ ማዕከል በታወቀ ምክንያት የጊዜ ገደብ ለውጥ ካልተገለጸ በስተቀር ለእያንዳንዱ የፕሮግራም ዓይነት በተፈቀደው ጊዜ መሠረት ፈተናው እንዲካሄድ ያደርጋል፤

በ. ፈተናው እንደተጠናቀቀ ተፈታኞች ፈተናቸውን በትክክል ማስገባታቸውን (Submit) ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል።

ተ. ተፈታኞች በሚቀመጡባቸው መቀመጫዎችና ኮምፒውተሮች መካከል በቂ ርቀት መኖሩን ያረጋግጣል፤

ቸ. በፈተና ጣቢያ አስተባባሪው የሚሰጠውን ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ያከናውናል።

## 8.3 ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ድጋፍ አድራጊዎች

ሀ. የፈተና ቀናት እና የሚሰጥበትን ፈረቃ መሰረት በማድረግ የአካል ጉዳተኛ ድጋፍ አድራጊዎች ይመደባሉ፣

ለ. በአንድ የፈተና ጣቢያ ለአንድ ዓይነ ስውር ተፈታኝ አንድ አንባቢ መምህር ወይም ሌላ አንባቢ ይመደባል፣

ሐ. የእጅ እንቅስቃሴ ችግር ያለበት ተፈታኝ ሲኖር በዩኒቨርስቲው በኩል ተረጋግጦ ሲቀርብ አንድ አንባቢ (ጸሀፊ) ይመደብለታል።

መ. አንባቢው ተፈታኝ ተማሪው በድጋሚ እንዲነበብለት በጠየቀ ጊዜ የተመደበውን ሰዓትና ቀጣዩን ፈተና ግምት ውስጥ በማስገባት ደጋግሞ ማንበብ ይኖርበታል፤

ሠ. አንባቢው ዓይነ ስውር ተማሪው ለፈተና ምቹና ከአዋኪ ቦታ (በረንዳ፣ መተላለፊያ ኮሪደር ወዘተ) የራቀ ቦታ እንዲፈተን ያደርጋል።

ረ. አንባቢው ተፈታኙ ለእያንዳንዱ የፈተና ጥያቄ የሚሰጠውን መልስ በከፍተኛ ጥንቃቄ ምልክት እያደረገ ወይም እየመረጠ ይሰራል፣

ሰ. በተቋሙ የሚፈተኑ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ቁጥርና የጉዳት ዓይነት ቀድሞ ለትምህርት ሚኒስቴር በማሳወቅ በህግ የተቀመጠውን ተጨማሪ ሰዓት እንዲያገኙ ያደረጋል፣

ሸ. ለዓይነ ስውራን እና የመጻፍ እክል ለገጠማቸው ተፈታኝ ተማሪዎች ለአንድ ሰዓት ቆይታ 15 ተጨማሪ ደቂቃ ይጨመርላቸዋል። ይህም ፈተናው ለሚወስደው ሁለት ሰዓት 30 ደቂቃ ተጨማሪ የሚኖረው ሆኖ ከሁለት ሰዓት በላይ ለሚወስድ ፈተና 40 ተጨማሪ ደቂቃ ይኖራል።

## 9. የመረጃ ልውውጥ

ሀ. በአጠቃላይ ሁኔታ የዩኒቨርሲቲ የመውጫ ፈተና ግብረ-ኃይል በትምህርት ሚኒስቴር ከተደራጀው ግብረ-ኃይል ጋር ግንኙነት በማድረግ ወጥ አሰራርን ይከተላል።

ለ. አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተደራጀ ንዑስ ግብረ-ኃይል ጋር እየተገናኙ በቅርበት ይሰራሉ፣

ሐ. የተፈታኝ ተማሪዎችን መረጃን ከሶፍትዌርና ሲስተም ጋር ተያይዘው በሚነሱ ጥያቄዎችና ጉዳዮች ከትምህርት ሚኒስቴር አቶ ባሲሊዮስ ጥላሁን (0911790912) እና አቶ እዮብ ሙሉዓለም (0922862478) ማግኘት ይቻላል።

መ. አጠቃላይ የፈተና አስተዳደርና አሰራር ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ጥያቄዎችና ሃሳቦች አቶ ሰይድ መሀመድ (0948862297) እና ዶ/ር እዮብ አየነው (0948862318) ማግኘት ይቻላል።

## 10. ክፍያን በተመለከተ

ሀ. ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራር ጋር በተደረሰው ስምምነት መሰረት በትምህርት ሚኒስቴር በኩል በሚከፈት ባንክ ሒሳብ ቁጥር (በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ) ተቋማት ባስፈተኗቸው ተማሪ ቁጥር ብዜት ገቢ የሚደረግ ይሆናል።

ለ. ተቋማት የሚያስፈትኑት የተማሪ ቁጥርን እንዲሁም በማዕከል የወጣውን ወጪ ታሳቢ በማድረግ ቀሪው እንዲከፋፈል ይደረጋል/ በውስጥ ገቢ አካውንት ይተላለፋል።

ሐ. ከማዕከል የሚተላለፈው ገንዘብ በፈተናው ለተሳተፉት ሙያተኞች ክፍያና ለተጓዳኝ ሥራዎች ወጪ መሸፈኛ ይውላል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

## 11. ተጠያቂነት

ይህንን የመውጫ ፈተና ሂደት እንዲደናቀፍ ያደረገ፣ ከሚጠበቅበት ሚና ውጭ ሲሰራ የተገኘ፣ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ፣ አጠቃላይ የፈተና ደንብ ጥሰት የፈጸመ፣ ማንኛውም አካል በዩኒቨርሲቲው አስተዳደራዊ ህግ መሰረት የእርምት እርምጃ ይወሰድበታል። ከዚህ በተጨማሪም እንደጥፋቱ ዓይነት (ክብደትና ቅለት) ጉዳዩ በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊደረግ ይችላል።

## 12. የማንዋሉ ተፈጻሚነት

ይህ ማንዋል ከሐምሌ 2015 ዓ.ም ጀምሮ በሚኖሩ የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ላይ ተግባራዊ ይደረጋል።

ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

የትምህርት ሚኒስትር

ሰኔ 2015 ዓ.ም